# በሃገራዊ የሠላም ድርድር ሂደት የሴቶች ተሳትፎ ላይ የተሰጠ ጋዜጣዊ

## መግለጫሰኔ 24፣ 2014 ዓ፣ም

## አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ ላለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚነሱ ግጭቶች፣ተፈጥሮአዊ የአደጋ ክስተቶች ሰላም እና ደህንነት በከፍተኛ ሁኔታ ተሸርሽሮ አሁን ላለንበት የህልውና ጥያቄ ዳርጎናል።በዚህም የግጭት ሁኔታም ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ የችግሩ ገፈት ቀማሾች መሆናቸው ይታወቃል። የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና ሌሎች የሰበዓዊ መብት ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች ያወጣው ሪፖርት መሰረት ሴቶች ፆታን መሰረት ያደረገ ከግጭት ጋር የተያያዘ ፆታዊ ጥቃቶች የተፈፀመባቸው ከመሆኑም በላይ ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋልጠዋል፣ ከቤት ንብረታቸው ከልጆቻቸው ተለይተው በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የተጠለሉ ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው።ከዚህ ጉዳት ጋር ተያይዘው የሚመጡ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ተፅኖዎች ለረጅም አመታት አብረዋቸው የሚዘልቁ ሲሆን በአገሪትዋ ደረጃ ይሄንን የአካላዊ፣ የስነልቦናዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በዘላቂ እና ቀጣይነት የሚያክሙ እና የሚያግዙ የመልሶ ግንባታ ውሳኔዎች እና አሰራሮችን መዘርጋት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ጊዜ የማየሰጥ ጉዳይ እንደሆነ እናምናለን።

የድርድር ዝግጅት በግጭት ተጎጂ ለሆኑት የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይም የችግሩ ከፍተኛ ገፈት ቀማሾች ለሆኑት ሴቶች ትልቅ እና ተስፋ ሰጪ እርምጃ ከመሆኑም በላይ ለሀገር ሰላምና ልማት ከፍተኛ እንደምታ ያለው በመሆኑ የምንደግፈው እርምጃ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን።

አ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ የሚደረጉ ዓለም አቀፍ የሰላም ድርድር ሂደቶች የተደራዳሪ ሴቶች ቁጥር 13% የደረሰ ሲሆን በአደራዳሪነትና በፈራሚነት የተወከሉ ሴቶች 6% ብቻ እንደሆነ ያሳያል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ተመሳሳይ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ሴቶች የተሳተፉባቸው የሰላም ድርድሮች የዘላቂ አፈፃፀም ሂደቶች የተሻለ መሆኑን ያሳያል።

ኢትዮጵያ ሴቶች በሰላምና ደህንነት ጉዳዮች ላይ ሊኖራቸው ስለሚገባ ድርሻና ጥበቃ የሚደነግገውን የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክክር ቤት ስምምነት የ1325ን ከ22 ዓመታት በፊት በሙሉ ድምፅ ካፅደቁት ሀገራት መሃል አንዷ እንደመሆኗ UNSCR 1325ን የሀገሪቱ የህግ ማዕፍቀ አካል ያደርገዋል። ከዚህም በtecehemari የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 6 እንደሚያሳዩት ሴቶች በማንኛውም ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ከወንዶች እኩል ተሳትፎና ውሳኔ ሰጪነት መብታቸው ተረጋግጧል::

ከጥቂት ወራት በፊት አዋጅ ቁጥር 1265//2014 የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን እንደ በጎ እርምጃ የሰላ ሂደት በመቀበል ኮሚሽኑን የሚመሩ እጬዎች በሚጠቀሙበት ወቅት አገሪቱን ህጎች እና የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እንዲሁም የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊነትን አጽንኦት በመስጠት ሴት እጩዎችን ጠቁመናል:: ሴቶች በእኩልነት የሚወከሉበት እና በቀጣይ ሂደቶችም በሚመረጡ ዓበይት ጉዳዮች መካከል የስነፆታ አጀንዳዎች እንዲካተቱ ጠይቀናል።በዚህ ተስፋ ሰጪ አቅጣጫ መሰረት የሴቶች ተሳታፊነት እና ውሳኔ ሰጭነት በብሄራዊ መግባባት፣ የሰላም ድርድር፣ እንዲሁም የሰላም ግንባታን ለማሳደግ ተያያዥ እና ተመጋጋቢ ስራዎችን በርብርብ በመስራት ላይ እንገኛለን።

ከዚህም አልፎ ጥምረት ለሴቶች ድምጽ በብሄራዊ ምክክር መድረክ በሚል 44 ድርጅቶች በአንድነት ተሰባበንና ቋቋቀመን ሴቶች በተጠናከረ መልኩ በብሄራዊ በምክሩ ላይ ለማተፍና አጀዳዎቻቸው ጎልተው እንዲወጡ ለመድረግ ከፍታኛ ዝግጅት በማድረግና ከብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር እየተነጋገርን እንገኛለን። ከዚህ ባለፈ በበላፈው ሳምንት የተቋቋመው ከፍታኛ የሴቶች ቁጥር የያዘው የኢትዮጵ ሴቶች ለሰለም ግንባታ

ቡድን  በማኅበረሰብ ደረጃ ግጭትን በመፈታትና በሰላም ግንባታ በንቁ እንዲሳተፉ የሚያስችል ነው ፡፡ በአጠቃላይ ሴቶች በባለፉት ዓመታት በነበረው ሁኔታ ግጭትና ጦርነትን በመቃወም፣ ሰላም እንዲሰፍን በመጠየቅ፣ ስለ ተጎጆዎች በመጮኽና ለተጎጂዎች ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደረጉ ቆይተዋል

ከዚህ አንፃር በቅርቡ ይጀምራል በተባለው በሁለቱ ዋና ዋና ተደራዳሪዎች ማለትም  በትግራይ ክልል እና በፌደራል መንግስት በሚደረግ ድርድር ዙሪያ እንዲሁም ወደፊት ለሚጀመሩ የሰላም ሂደቶች ጭምር የሚከተሉትን ጥያቂዎች ስናቀርብ ከሁሉም አካላት በጎ ምላሽ እና ትብብር መንፈስ ታሳቢ በማድረግ እናቀረባለን፡፡

1. **ለተከበራችሁ ዋና ተደራዳሪ አካላት**:
    - ባላፉት ሁለት አመታት የነበረውን ውጥረት፣ ግጭት፣ ጦርነት እና ረሀብን በተለይም በሴቶች እና ህፃናት ላይ ያደረሰውን ዘርፈ ብዙ አደጋ እና የደረሰውን ጥፋት ከግምት በማስገባት ከሁሉም በላይ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት ለድርድር ያሳያችሁትን ፍቃደኝነት እና ቅድመ ዝግጅት እንደገፋልን ፡፡
    - ከዚህም ተያይዞ ከላይ በመግቢያው በገለፅናቸው እና ኢትዮጵያ በሴቶች መብት ዙሪያ ባስቀመጠቻቸው ህጎች እና መርሆች አለማቀፍ ቃልኪዳኖች መሰረት በማንኛውም ደረጃ በዋናነት በከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካልት ደረጃ አንድ / Track1 ) በዋና ተደራዳሪነት ሴቶች እንዲወከሉ እንጠይቃለን፡፡ ከዚህ ተከትሎ በሚዋቀሩ ባለሙያ እና አማካሪ ቡድኖች ውስጥ ደረጃ ሁለት (track2)ውስጥ እንዲሁም በማህበረሰብ ደረጃ የሚደረጉ የስላም ግንባታ ሂደቶች ደረጃ 3 (track 3 ) የሰላም ድርድር እና ስምምነት እንዲሁም የሰላም ግንባታ ሂደቶች ላይ በእኩል ተሳታፊነታቸው እና ውሳኔ ሰጭነታቸው እንዲረጋገጥ በትኩረት እንድትሰሩ እንጠይቃለን፡፡
    - ይህም ጥያቄ ከወዲሁ በተለይም በቅርቡ እንደሚጀመር የሚታወቀው በከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪዎች ደረጃ የሚደረገው የሰላም ድርድር ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን በአፅኖት እንጠይቃለን፡፡
    - የሴቶች ተሳታፊነት እና ውሳኔ ሰጪነት ያላረጋገጠ ሂደት ውጤቱ አጥጋቢ እንደማይሆን ታውቆ የማኅበረሰቡ ከግማሽ በላይ የሆኑት ሴቶችን ድምፅ እና የስርአተ ፆታ እና የሴቶችን ጥቅም የሚያረጋግጡ ሀሳቦች እንዲካተቱ እንጠይቃለን፡፡
    - ከዚህም ጋር ተያይዞ ተደራዳደሪ አካላት በሙሉ በአደራዳሪነት የሚሾሙዋቸውን አሸማጋይና አደራዳሪ አካላት የሴቶችን እኩል ተሳታፊነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ እንጠይቃለን፡፡

2. **በተደራዳሪ አካላት በአባልነት እና በኃላፊነት የምትገኙ ሴቶች**

በሰላም ድርድር እና ተፈፃሚነት ላይ ሴቶች ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጭነት መጨመር እና ማረጋገጥ የሁሉንም ርብርብ ቢጠይቅም ለውጤታማነት እና ዘላቂነቱ ለማረጋገጥ የሴቶች አቅምና ውክልና ሚና የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ይህም በሁሉም ደረጃ በተለይም በመጨረሻ የፖለቲካ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍን ማረጋገጥ በየትኛውም ወገን የፖለቲካ ውሳኔ እና ሌሎች ልዩነቶች በዘለለ ሴቶችን በሴትነት ሊጋሩት እና በአንድ ላይ ሊያስፈፅሙት የሚገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡

እኛ በሲቪል ማህበራት የተደራጀን እንዲሁም በግል የቆምን ሴቶች ከተደራዳሪ አካላት ውስጥ በከፍተኛ አመራር ደረጃ የሚገኙ ሴቶች የሴቶችን አጀንዳ በማንሳትና ተፈጻሚነቱን እዲረጋግጥ እድትሰሩ በኢትዮጵያ ሴቶች ስም እንጠይቃለን፡፡ ይህንን ለማስፈፀም በምተዳረጉት ጥረት ሁሉ ለመተባበር ዝግጅታችንን እንገልፃለን::

3. **በኢትዪጵያ ውስጥ የምትሰሩ ሀገር በቀል የሲቪል ማኅበራት/ ድርጅቶች**

በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው የሰብአዊ መብት እንዲሁም የእኩል ተጠቃሚነት ርዕስ ጉዳይ ከሴቶች መብት ጉዳይ ተነጣጥሎ የሚታይና የሚፈፀም አይሆንም ውጤትም አያስገኝም ፡፡

- ይህ ጥሪ በሀገሪቱ ላይ በጠቀስናቸው በሰብአዊ መብት በዘላቂ ልማት እና ሰላም እንዲሁም እኩል ተጠቃሚነት ዙሪያ በአገሪቱ የምትሰሩ ሀገር በቀል አካላት በተጀመረው የሰላም ድርድር የሴቶችን ተሳታፊነት ውሳኔ ሰጭነት እና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲደረግ በምናደርገው ጥሪ ላይ ዛሬ እንዲሁም በዘላቂነት አብራችሁን እንድትቆሙ እና ርዕሱን እንድትደግፉት እንጠይቃለን፡፡

4. **የሚዲያ አካላት**

በማንኛውም ማህበረሰብ መስተጋብር ሰላም እና መግባባት እድገትን የሚያረጋገጠው በተለይም የማህበረሰቡ የደምስር በሆነው የሚዲያ ተሰትፎ ነው፡፡ የሚዲያ አካላትም በዚህ ወሳኝ የአገር ሰላም እና መልሶ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ አላቸው፡፡ በመሆኑ በቅርቡ የሚጠበቀውን በቀጣይነት የሚደረገውን yeሰላም የፖለቲካዊ ድርድር እና ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን ሂደቶች በበጎ እና ገንቢ ሁኔታ እንትዘግቡ እየጠየቅን፣
በተለይም እነዚህ ዘገባዎች ውስጥ የስርዓተ ፆታን ውክልና እና የውሳኔ ሰጭነት ቦታዎችን የሴቶች ተሳትፎን እና የሚታዮ ጉድለቶችን እና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በማጉላት በበኩላችሁ የሰላም ግንባታ አካል እንድትሆኑ እንጠይቃለን፡፡

5. **ዓለም አቀፍ አካላት**

የኢትዮጵያ ሰላም በዋናነት እንዲሁም በባለቤትነት የሚረጋገጠው በኢትዮጵያዊያን በተባበረ አቁዋም መሆኑን ይታወቃል፣በዚህ ዘላቂ ሰላም ግንባታ ዙሪያ በተለያዩ ደረጃ የሚደረጉ ጅማሬዎች በተለይም በከፍተኛ ውሳኔ ሰጪዎች (ደረጃ 1 track 1) የሰላም ድርድር እና ስምምነት ላይ በአለም አቀፍ ደረጃ እንደሚታየው ዝቅተኛ የሴቶች ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጭነት በአገራችንም ይታያል:: በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ በሚደረገው የሰላምና የፓለቲካ ድርድር ሂደት ውስጥ በአሸማጋይነት እና በአማካሪነት እንዲሁም በተለያየ አግባብ የምትሳተፉ አካላት(የአፍሪካ ህብረት የተባበሩት መንግስታት የጎረቤት ሀገራት እንዲሁም እስከዛሬ በነበረው ሂደት ድጋፍ ያደረጋችሁ አካላት በቀጣይነት በሚኖራችሁ ድርሻ መሰረት በሰላም ድርድሩ የሴቶች ተሳትፎ እና ውሳኔ ሰጭነት ማእከላዊ ጉዳይ ሆኖ እንዲቀጥል እና እንዲረጋገጥ እገዛ እንድታደርጉ እንጠይቃለን ፡፡

6. **የኢትዮጵያ ወንዶች አጋርነት**

እኛ በኢትዮጵያ በሴቶች መብት ላይ የምንሰራ የሲቪል ማኅበራ ይህን ማስታወሻ እና ማሳሰቢያ ለዘላቂ ሰላም እና የእኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የምናደርገውን ትግል የኢትዮጵያ ግማሽ አካል የሆኑት የወንዶችን አጋርነት ከፍ ያለ ቦታ እንደምንሰጠው ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

በመጨረሻም የሰላምን አስፈላጊነት በጽኑ ተረድተን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በያለንበት በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን እና የሴቶች ተሳትፎ በሰላምና ደህንነት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ጥያቄያችንን እናቀርባለን ፡፡

## የሲቪል ማህበራት ዝርዝር

1. የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት
2. የአማራ ሴቶች ማኅበር
3. አዲስ አበባ ሴቶች ማኅበር
4. ትምራን
5. የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
6. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል
7. ሃገር ዓቀፍ ሴት ወጣቶች በጎ አድራጎት ድርጅት
8. ቃል የተቀናጀ የሴቶች ማኅበር
9. ሴቶች ይችላሉ
10. ጉድ ሰማሪታን ማኅበር
11. የኢትዮጵያ ሴት አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማኅበር
12. የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ተሟጋች
13. ቤንሻንጉል ሴቶች ማኅበር
14. ኢምፓቲ ፎር ላይፍ ኢንትግሬትድ ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን
15. ስብሰብ ለሰባዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ
16. ጌት ፎር ኦፖርቹኒቲ
17. ሲቄ የሴቶች ልማት ማኅበር
18. ኮንሰርን ፎር ኢንትግሬትድ ዴቨሎፕመንት
19. የኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ማኅበራት ኅብርት
20. የኢትዮጵያ ሴቾች ለሰላም ግንባታ
21. ጥምረት ለሴቶች ድምጽ በሃገራዊ ምክክር መድረክ
22. ፕሮጃይኒስት
23. ሙዳይ የአርዳታ ድርጅት
24. ድሬደዋ ሴቶች ማህበር
25. ሁሪካ ማህበር
26. ተርካንፊ
27. ሴታዊት
28. አናራ ማህብር
29. አንቁ ታበራ ዎመን ኢንፓወርመንት
30. ቤዛ ማህበር
31. አጋር ኢትዮጵያ
32. አክሽን ለኢትዮጵያ ደስታ
33. ሴንተር ኦፍ ኮንሰርን
34. በሩህ ማይንድስ ማህበር
35. አዶይ ሴንተር ለኢትዮጵያ
36. የአናቶችና የህጻናት ማገገሚያ ድርጅት
37. ፋምሊ ሰርቪስ ማህበር

38. ናሽናል ያንግ ዎመን ማህበር
39. ቪኢካድ ማህበር
40. ሃረማያ ዮኒቨርስቲ የሴቶች መሪ አማካሪ
41. አልባት የአርዳታ ድርጅት
42. ኤጉማፊ ማህበር
43. ኦርጋናይዜሽን ፎር ገርልስ ኤንድ አድቮካሲ
44. ፎረም ፎር አፍሪካ ውመን አኢዱኬስናሊስት
45. ስቱደንት ጌም ቼንጀር
46. ኢንተግሬትድ ፋምሊ ሰርቪስ ማህበር
47. ሴንተር ፎር ኢንሼቲቭ ኤንድ ዲቬሎፐመንት
48. ኦሞ ሞርኒንግ ስታር ቺልድረን

የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ተሟጋቾች

1.ሳምራዊ ጣሰው

2. ልደት ተካ

3 አለምጸሀይ ወልደማርያም

ADOYE
CENTER FOR ETHIOPIAN WOMEN EMPOWERMENT

ACTION FOR HAPPINESS ETHIOPIA

Agar Ethiopia
Respond! Renew! Rebuild!

AHRE

OMO'S MORNINGSTAR CHILDREN

CAFOD SCIAF Trócaire
CST Working Together

CFID

Center of Concern

DIRE DAWA ADMINISTRATION WOMEN'S ASSOCIATION

EHRDC

Ethiopian Women Lawyers Association

FAWE - Ethiopia Chapter

HARAMAYA UNIVERSITY'S FEMALE LEADERS & ACADEMICIANS NETWORK

FAMILY SERVICE ASSOCIATION

FEAPD

ቃል Kal

MCRC
Mother and Child Rehabilitation Centre

N4ED
NUTRITION 4 EDUCATION & DEVELOPMENT

NATIONAL YOUNG WOMENS' CHARITY ORGANIZATION

NMW
New Millennium Wome
Empowerment Organiz

OMO'S MORNINGSTAR CHILDREN

OGAA

ፕሮጂኒስት
PROGYNIST

ሴታዊት
Setaweet
ለፆታ እኩልነት

Union of Ethiopian Women and Children Associations
UEWCA

ቪኢኮድ
VECOD